# ኮለኔል አስናቀ እንግዳ: ስራቸውን ጨርሰው ያረፉ ጀግና

ኢያሱ ዓለማየሁ

እውነቱን ለመናገር ኮለኔል አስናቀ እንግዳ ሞቱ ማለት ትክክል አይደለም። መስራት ያለባቸውን ሰርተው፤ ለሀገራቸው መከራና ችግርን ችለው፤ለሚወዱት ሕዝብ ሕይወታቸውን ለመስጠት ተጋፍጠው፤ ለብዙዎቻችን አርአያ ሆነው፤ የልጅ ልጅ አይተው፤ ሀገራቸውን አኩርተው፤ ለማንም ሰብዓዊ ፍጡር ተንበርካኪ ሳይሆኑ፤ ኢትዮጵያን አስቀድመውና ማንም ዜጋ ከሚሸከመው በላይ ተሸክመው፤ ታግለውና አታግለው ወደማይቀረው የመጨረሻ ዕረፍት የሄዱ ናቸው።



ለጀግና አያለቅሱም ተብሏል። ጀግኖች ሞትን አይፈሩምና ዘጠኝ ሆኖ ቢመጣም አንድ በአንድ ግባ የሚሉ ናቸው። የጀግና ጀግና፤ የወርቅ ዜጋ ምሳሌ የነበሩት ኮለኔል አስናቀ ስለ ታሪካዊ የሕይወት ሂደታቸው በመጽሃፍ አስፍረውታል። እኔ ስለ እሳቸው ማለት የምፈልገው በትግል ሜዳ በጎንደር ካገኘኋቸው ጀምሮ ለእኔ ለግሌ፤ ለድርጅቴ ለኢሕአፓ፤ ለኢትዮጵያና ለትግላችን ምን እንደምታና ሚዛን እንዳላቸው ምስክርነትን ለመስጠት ግዴታ ስላለብኝ ነው። ኮለኔል አስናቀ እኛ ኩታሮች ሳለን፤ ለንቃትም ለተቃውሞ ሰልፍም ገና ሳንበቃ ዛሬ ታሪክን ማጤን ያቃታቸው የሚያመስግኑትን የዘውድ አገዛዝ ተቃውመው፤ በአፍ ብቻ ሳይሆን በተግባር አጼውንም ለመገልበጥ የጣሩና የእስር ስቃይንም የተቀበሉ ናቸው። ወዳጃቸው ኮለኔል እምሩ ወንዴም ተመሳሳይ የሚያኮራ ታሪክ አላቸው። ሁለቱም በአጼው ስርዓት በደል ለደረሰበት ሕዝብ መብትና ብልጽግናን ለማምጣት መስዋዕትነትን የደፈሩ ናቸው። ከእነሱ በኋላ ነቃን አወቅን ብለን የተነሳነው ወጣቶች አርአያ የሆኑልን ኮለኔል አስናቀና መሰሎቻቸው ናቸው። ኮለኔል አስናቀ የሀገራቸውን ድንበር ለማስከበርም በጦር ሜዳ የዋሉ ቆፍጣና መኮንን መሆናቸውም መጠቀስ ያለበት ነው ።

ኮለኔል አስናቀ (ና ኮለኔል እምሩ) በቀውጢ ጊዜ በኢሕአፓ አባልነት ተሰልፈው ብዙ አስተዋጾ ያደረጉ ናቸው። አፈናውና ሽብሩ አይሎ አስጊ ሲሆንም ወደ ትግል ሜዳ ዘልቀው ሰራዊቱን መቀላቀላቸው ይታወቃል። የኮለኔል አስናቀ ጽናትና

ቆራጥነት ለብዙ ታጋዮች ምሳሌ እንደነበር ከግል ተመክሮዬም የማውቀው ነው። ሀገሬውን በመቀስቀስና በማደራጀት የሰጡት ግልጋሎት ከፍተኛም ነበር። በሱዳን መሬት በምስጢር ስምሪት ኮለኔል አስናቀ የፈጸሙት ጀብድ የታሪክ መኪና ጎማ ከማረፊያ ቦታው ስላልደረሰ በዝርዝር ባይነገርም የምናውቀው እናውቃለን። እንዲህ በጥቅሉ ሲቀርብ የእሳቸው ጀብድና ማንነት ነፍስ ይዘቱ ሊንጸባረቅ አይችልም። ኮለኔል ግን በሁሉም የሚወደዱ፤ መወላወልን የማይወዱ፤ ጨዋታንም የሚያውቁ ነፍስና ለዛ ያላቸው ታላቃችን ነበሩ። ለአድር ባይ ትዕግስት ያልነበራቸው በመሆኑና ፈሪንም ማስጠጋት የማይፈልጉ በመሆናቸው በባሕርይ የተስማማን "አክራሪዎች" ነበርን ማለትን እደፍራለሁ። የድርጅቱ ጠላቶች ሊነጥሉትና ሊያጠቁት ሲነሱም ሀገር ወዳድ በሚል መሰረትን አስፍቶ ትግልን ማገዝ ሲባልም እሳቸውም፤ ኮለኔል እምሩም ሀገር ወዳድ በሚል ሰፋ ያለ ተቋም ተመስርቶ መንቀሳቀስ የሚለውን ሀሳብ ተቀብለውና ደግፈው በዚሁም መሰረት ለመንቀሳቀስ የተሰጣቸውን ግዳጅ ያሟሉ ነበሩ። ዛሬ መለስ ብለን ስናይ ያን ክፉ አገዛዝ የሚያወድሱ ያውም ወጣትና ነን የሚሉ ባሉበት እነ ኮለኔል አስናቀ ግን ኋላ ቀሩንና ጨቋኙን ስርዓት ይዘት አውቀውና ነቅተውብት ሊገለብጡት ቆርጠው መነሳታቸው እንደምታውም ቀላል አልነበረም። ኮለኔል አስናቀ አርበኛም ጀግናም ነበሩ ግን ጊዜ ሲቀየር ደግሞ ጦር ጋሻቸውን አልሰቀሉም። ጣሊያን ሲወረን አርበኛም ባንዳም የነበሩትን እናውቃለን። አጼው ምድረ ባንዳውን ሾመዋል። አርበኞች የነበሩትም የጨቋኙ ስልጣን ተባባሪም ደጋፊም ሆነው ለውግዘትም ለሞትም በቅተዋል። ታከለ ወልደ ሐዋርያትና አበበ አረጋይ ጉዞአቸው አንድ አልነበረም። ኮለኔል አስናቀ በአጼው ጨቋኝ አገዛዝ ላይ ተነስተው ይህ በቃ በሚል ለደርግ ተንንባሽ አልሆኑም። ደርግ ሲመጣ ኮለኔል ጽኑ ጸረ ደርግ ሆነው ትግላቸውን ከኢሕአፓ ጋር ቀጥለዋል። ጥቅም ፈልገውና ተስፋ ቆርጠው ለባለ ነፍጥ እጅ የሰጡ ሳይሆኑ ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና ክብር ትግል የቀጠሉ ጀግና ነበሩ። ከየካቲት 1966 በኋላም የኮለኔል አስናቀ ታሪክ ከኢሕአፓ ጋር ተጣምሮ የሚቀርብ መሆኑ ለድርጅቱ የሚያኮራ ሆኖ የሚገኝ ነው። ኮለኔል አስናቀ ጽኑ ጸረ ወያኔና ጸረ ጎጠኞች ሁሉ ሆነውም ቆይተዋል።

ወናፎች ሁለት አፍ አላቸውና ኮለኔል አስናቀን ከኢሕአፓ ለመነጠል ብዙ ከንቱዎች ጥረው ከሽፎባቸዋል። ዛሬም ውድቅ በሆነ ጥረታቸው መግፍታቸው የሚጠበቅ ነው። ከ1966 በፊት ኮለኔል በሚያኮራ ቆራጥነት ለህዝብና ለሀገር የታገሉ ቢሆንም ከየካቲት 1966 ወዲህ ደግሞ ኢሕአፓ ሆነውና የነበረውን የለውጥ ማዕበል እየቀዘፉ የታገሉ ንቁ ጀግና ናቸው። በማይጠበቅ ደረጃ--ከዕድሜያቸውና ካደጉበት ሁኔታ አንጻር-- ተራማጅ አቅዋሞችን አቅፈው ወደፊት ያሉ ናቸው። ኮለኔል አስናቀ ስለ ሴቶች ብሶት የጻፉትን ያጤኗል። ከማንም በፊት የአካባቢ አክራሪዎችና የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶችን አደጋም መጽሃፍ ጽፈው ጠቁመዋል፤ አስጠንቅቀዋል። ኮለኔል አስናቀ ተግባራዊ ምሁር ነበሩ። የፈረንጅ ሰነድና ሽልማት ባይደቅኑብንም ታታሪ ምሁር ከሚሰራው በበለጠ መጽሃፍት በማቅረብ እያከታተሉ ትምህርት ሰጥተውናል። ይህን በተመለከተ ጽናቱን እንዴት እንዳገኙት ስጠይቃቸው ሁሌም እየሳቁ "ዛሬ እንደእናንተ የትግል ውጣ ውረድ የለብኝ፤ ጊዜ አለኝ" ይሉ የነበረውን አስታውሳለሁ። ስንቱ ጊዜ ያለው ባክኖ መቅረቱን ስለማውቅ ምላሻቸውን አለተቀበልኩትም። በተጨማሪም በእሳቸው ዕድሜ ያሉ ወይም አዛውንት የሆኑና ምሁር በሉን ባዮች ከንቱዎች ሽበታቸው የእንጨት ሆኖ እስካዛሬ የኢትዮጵያን ታሪክ የከሸፈ የሚሉና ህዝባችንን የሚዘልፉ መኖራቸውን ስገነዘብ ለኮለኔል አስናቀ አክብሮቴ የሚጨምር መሆኑ አልቀረም። እሳቸውን በተመለከተ ዕድሜ ጸጋም ክብር ነው፤ ለሌሎች ግን ውርደትን አጃቢ ሆኖ ተገኝቷል ።

ኮለኔል አስናቀ ህይወታቸው ከኢሕአፓ የተያያዘ መሆን ማንም ሊሰርዘው የሚችል አይደለም። እሳቸውና ድርጅታቸውን ሲያጣሉ የጣሩ ጥቂቶች አልነበሩም--ግን አልተሳካላቸውም። ዛሬም ታሪክን ሊክዱ ቢፍጨረጨሩ ሰሚ የሚያገኙ አይሆንም። ከኢሕአፓ ጎን ሆነው የታገሉ ሲያርፉ ይህን አኩሪ ታሪካቸውን ሊሰርዙ የሚጥሩ ተምቾቾን በፊትም ታዝበናል። የራሳቸውን ባንዳነትና ክህደት ለመሸፈን መሆን አለብት በሚል በበኩሌ ከደመደምኩት ዓመታት አልፈዋል። ኮለኔል አለማየሁ አስፋው (ተበጀ) ሲያርፍም ኢሕአፓ እንደነበር ለመደበቅ የተደረገው ጥረት የሚረሳ አይደለም። ለምን? ለምን ታሪክ ይደበቃል፤ ይሰረዛል? ኢሕአፓን የከዱ ብዙዎች ናው-- ኮለኔል አስናቀ ግን ከዚህ ዝርዝር አይገቡም። የእኔም ምስክርነት ይህን ይመለከታል። ኢሕአፓ ሆነው የነበሩና ግን የተዉትና በጠላትነት የተሰለፉት ራሳችውን ጻንተው ከቆዩት ከኮለኔል አስናቀ ጋር ሲያወዳድሩ ዝቅተኝነት ይሰማቸዋል። ይቀናሉ። ሐፍረት ይውጣቸዋል። ኢሕአፓም እንደ ድርጅት እስከ መጨረሻው ለኮለኔል አስናቀ የሰጣቸው አክብሮት ያንገብግባቸዋል። ታሪክ ግን ታሪክ ነው። ስም ከመሬት በላይ የሚቆየው አኩሪ ታሪክ ሲሰራበት ነው፡፡ በዚህ ረገድ የአኔ ታላቁ ሳሙኤል ዓለማየሁ ባረፈ ጊዜ ሜሪላንድ መድሃኒያለም የበዓልና የባህል ነጭ ልብስ ለብሰው የመጡበትን ጊዜ አስታውሳለሁ። ንግግራቸው በቀጥታ ለእናቴ ነበር። ዛሬ የደስታ ቀን ነውና አታልቅሺ። እኔ የበዓል ልብስ የለበስኩት የደስታ ቀን በመሆኑ ነው። ሳሙኤል ቃል ኪዳኑን አክብሮ ነው ያረፈው። ከድቶ ሳያሳዝንሽ፤ ሳያሳፍረን ጻንቶ እንደታገለ አርፏል። ይህ ያስደስታል እንጂ የሚያስለቅስ አይደለም። የምናለቅሰውማ ዓላማውን ስቶ፤ ከድቶ ቢያዋርደን ነበር" ብለዋል። የእኛ ኮለኔል አስናቀ እኚህ ነበሩ።

ኮለኔል አስናቀ ከሀዲ አይወዱም። ያደጉበት ሁኔታ ለባንዳ ትዕግስትን አላስተማራቸውም። መፈንቅል ሙከራቸው በከሃዲዎችም መጋለጣቸውን መቸም የረሱ አልነበሩም። ሀይማኖተኛ ነበሩና ቃል ኪዳናቸውን አክብረው እስከ መጨረሻ ይዘው ቆይተዋል። ሀቀኛ ኢትዮጵያዊ ነበሩና በሀገር ላይ መቸም አልተደራደሩም። በኢሕአፓ ሠራዊት አስከፊው የብተና አደጋ ሲከሰትም ኮለኔል አስናቀ ከኢሕአፓ ጎን ቆመው አብረታተውናል። የተበተኑት እንደማይመለሱ ሲረዱም በዚያን ወቅት የነበርነውን አመራሮች የተቀበረውን የጀግኖች ደም የፈሠሰበትን መሳሪያ አውጥተው ሀገር ወዳጆችን ሊያታግሉበት ጠይቀውን ይሁን ብለናቸው ይህን የሰማው የብተናው ቁንጮ አንድ ዛሬ በአሜሪካ ነዋሪ የሆነ የቀበራውን ቦታ የሚያውቅ ጋሻ ጃግሬውን ወደ ሱዳን ወታደሮች (ባሶንዳ) ልኮት ወታደሮቹ ኢትዮጵያ መሬት ገብተው መሳሪያውን ወስደውታል። ኮለኔል ይህን በተመለከተ ቁጭታቸውንና ንዴታቸውን በዝርዝር በመጽሃፋቸው አስፍረዋል። (በነገራችን ውሎ አድሮ ትግሉን ቀጥለን ሱዳን የወሰደብንን መሳሪያ ማስመለስ የቻልን ቢሆንም ለደረሰው ጉዳት የነበረን ንዴትን ተቃውሞ ይህ የብተናው ቁንጮ ወደ ወያኔ ገብቶ ቆይቶ በቀይ ሽብር ላይ ፊልም ሰርቻለሁና ተመልከቱልኝ ብሎ በዋሺንግተን ለእኔም ለእሳችውም ግብዣ ሲልክ ተነጋግረን አንሄድም ብለን ቀርተናል)። ኮለኔል ወያኔ ስልጣን ከያዘ በኋላ ጉባኤ አበው የሚል መስርተው የአዛውንት ጥረቶችች አንቀሳቃሽና ተካፋይ በመሆን ድርጅቶችን ለማስታረቅ፤ በተባበሩት መንግሥታት የኤርትራን መገንጠል በመቃወም፤ ጸረ ወያኔ ህብረቶችን በመደገፍ ወዘተ ከትግሉ ጎን ቆመዋል። በየጊዜው የኢሕአፓ የክብር እንግዳ በመሆን በየስብሰባውም ተገኝተዋል። ዕድሜያቸው ገፍቶ ባለበትም የሌላ የአንጃ ጥቃት በውጭ ሀገሮች ሲደርስብንም ባይከሰት ኖሮ ደስ ባለኝ፤ ከወያኔ እኮ የሚገኝ ምንም የለም፤ ለመታረቅ ሞክሩ፤ ቃል ኪዳናችሁን አክብራችሁ ግን ቀጥሉ ታገሉ በሚል ነው ለእኔና ለጓዶቼ ምክር የለገሱን። ህመም እየጸናባቸው ሲሄድ ሳይቀር ዛሬ እናንተ ድጋፍ በሚያስፈልጋችሁ ጊዜ ደከምኩ የሚል ቁጭትንም ያሰሙ ነበር፡፡ ኮለኔል አስናቀ ስል ይህን ሁሉ አስታውሳለሁ። ሳላቋርጥና

ሁኔታው በፈቀደበት ከቤታቸው በመሄድ፤ ከፓሪስም በመደወል ያጫወትኳቸው፤ ያነጋገሩኝ ሁሉ ዛሬ የማከብረው ትዝታዬ ነው።

ኮልኔል አስናቀን ልዩ የሚያደርጋቸው የዕድሜ ባለጸጋ (ከመቶ ዓመት በላይ) ቢሆኑም ጊዜ አልገታቸውም። የጭቆና አገዛዞችን ሳያቁርጡና ተስፋ ሳይቆርጡ ታግለዋል። የአድሃሪም አንድ አጥንት አልነበራቸውም--የስር ነቀል ለውጥ ደጋፊ ነበሩ እንጂ። አብዮተኛ ነን ብለው በየፌርማታው ሽብረክ ያሉና ክህደትን ያቀፉትን ስናይ እውነትም ኮለኔል ልዩ ሰው ነበሩ። ስንቱ ኢሕአፓን ሲከዳ፤ ውጣ ውረዱ ሲያይል ስንቱ በድርጅቱ ላይ ሲነሳ ኮለኔል አስናቀ በርቱ ታገሉ እንጂ እጅ ስጡ፤ በቃ ሲሉም አለመደመጣቸው ጸጋ ነው። ኮለኔል እንደሚጠበቀው ብዙ ጠላቶች ነበሯቸው። ቃል ኪዳኑ ያከበረና ለኢትዮጵያ የቆመ ሁሉ ጠላቶቹ ብዙዎች ናቸው። ደርጉ፤ወያኔው፤ ገንጣዩና የባዕድ ቅጥረኛው ብቻ ሳይሆን የአጼውም አገዛዝ አፍቃሪዎችም የሚወዷቸው አልነበሩም። እሳቸው ግን ይህ ሁሉ በያዙት እንዲቀጥሉ አበረታታቸው እንጂ አላዳከማቸውም። የዚህ ምስክሩ ደግሞ ከኢሕአፓ ጎን ጸንተው መቆማቸውና መቀጠላቸው ነው። የሰጡን ያልተቋረጠ ድጋፍ ነው።

ኮለኔል አስናቀ ኢሕአፓ በጽሁፉና በራዲዮው የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በጣሊያኑ ወራሪ ቋንቋ ባንዲራ ማለት የለበትም ሲሉ ከጠዋቱ የሰጡንን ማሳሰቢያም አልረሳንም እንላቸዋለን። መጽሃፍ ማንበብ የሚወዱና የዕውቀት ድንበራቸውን ሊያሰፉ የሚጥሩም ነበሩ። በአንድ የዋሺንግተን ይፋ ስብሰባ ላይ አብሮአቸው የተገኘውን ሟቹ ፕሮፌሰር መስፍን አርአያን አንስተው ለእኔ የምሁር ምሳሌ እሱ ነው፤ በውልደት ኤርትራዊ ቢሆንም ኢትዮጵያዊነቱን አስቀድሞ ሻዕቢያን ተቃውሟል፤ የመጣበትን ውግዘትና ወከባ ፈርቶ አልተሸነፈላቸውም ያሉትንም ሳስታውስ የኮለኔል መሰፈርት ምን እንደሆነም እንድገነዘብ አድርገኛል። ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ላይ የዘመቱ ከሀዲ ሊባሉ የሚገባቸውን ባለ ታፔላዎችና ወንጀለኞች ክብር ለሚሰጡትም ምክር ሊሆናቸው የሚችል ነው።

ሳይንስ ብዙ ቢራመድም የማይቀረውን የመሄጃ ግዜ  መሰረዝ የሚቻል አይደለም። ብዙዎቻችን የኮለኔልን ዕድሜ ብናገኝ በታደልን ነበር። ኮለኔል አስናቀ በተቀበሩበት ሀሙስ የ 92 ዓመት አክስቴም አርፋ ተቀብራለች። የሕይወት ሂደቷ የእሳቸውን ባይመስልም በሴትነቷ፤ በእናትነቷ፤ በኢትዮጵያዊነቷ የራሷን ከባድ መስቀል ተሸክማ የኖረች ነበረች። ትንሺቷ ልጇን እሌኒን ና የእህቷን ልጅ የእኔን ወንድም ዳዊትን ደርግ ገድሎባታል ።

ለሁሉም መሬቱ ይቅለላቸው።

ኢሕአፓም ኢትዮጵያም በኮለኔል አስናቀ ማረፍ ተጎድተዋል።

የምንገባላቸው ቃል ኪዳን ግን  የተጀመረውን ትግል እስከ መጨረሻው ድረስ የምንቀጥል መሆናችንን ነው።

ትግሉን ቀጥለው ጨቋኞችን የሚያርበድብዱ እስካሉ ድረስ ጀግኖች ቢያርፉም ሕያው ናቸው!!